በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራያዊ ሪፐብሊክ

የጠቅላይ ፍርድ ቤት

የ2014 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት/2015

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራያዊ ሪፐብሊክ

የጠቅላይ ፍርድ ቤት

የ2014 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

የጠቅላይ ፍርድ ቤት የተመደበለትን የመደበኛ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን ዓለም አቀፍ የዋና ኦዲተሮች የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑንና በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች ፤ መዛግብት፤ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በቴያትር ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የተጠቃለለ ሂሳብ ማመዛዘኛ፣

<u>ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣</u>

የጠቅላይ ፍርድ ቤት የ2014 የሂሣብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁና፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን ጠብቆ የተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

<u>ገቢ</u>

1. በፋይናንስ አዋጅ ቁጥር 970/2008 የፌዴራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 2 ማንኛውም በመንግስት ስም የተሰበሰበና ቀጥታ ወደ መስሪያ ቤቱ ወይም ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት ገቢ መደራግ ያለበት የመንግሥት ገንዘብ በተሰበሰበበት ዕለት እንደአግባብነቱ ወደ መስሪያ ቤቱ ወይም የማዕከላዊ ግምጃ ቤት የባንክ ሂሳብ ገቢ መደረግ እንዳለበት በተደነገገው መሰረት ተግባራዊ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ በተወሰደ የኦዲት ናሙና ፤ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰኔ 30/2014 በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ላይ በሂሳብ መደብ 1422113 (1415) በዳኝነት የተሰበሰበ ብር 341,512.91 ከልዩ ልዩ ምንጮች የተሰበሰበ ቢሆንም የዳኝነት የሚሰበሰበው ገንዘብ በበጀት ዓመቱ በፍርድ ቤቱ በዳኛ ውሳኔ መሰረት ብር 307,361.62 በተመለሸ ወጪ የሂሳብ ቁጥር 2821107 ለባለመብቶቹ የተመለሰውን የገንዘብ ተመላሽ ተደርጎ እና 10% የክርክር ወጪ ተቀናሽ ተደርጎ ሲከፈል ብር **34,151.29** በትራንዛክሽን ሠነድ የተቀነሰው ገንዘብ የማይታይና ምዝገባ ያልተደረገ እና መረጃ ደጋፊ ሠነድ የሌለ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

<u>ተከፋይ</u>

2. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 በፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 5 በተመለከተው መሰረት ተከፋይ ሂሳቦች ለጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ጥቅም የዋሉና ትክክለኛ ዕዳዎች መሆናቸውን ለመከታተል የሚያስችል ተገቢው የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋቱንና ሂሳቡም በወቅቱ መከፈሉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተከፋይ ሂሣብ ሪፖርት ከሚታየው ሂሳብ ውስጥ ፤

- በሂሳብ አርእስት 6174202 (5052) ከዚህ ውስጥ በዳኛ ትዕዛዝ የሚከፈል የግለሰቦችና ድርጅቶች የተያዘ ብር 1,013,809,299.24 ባለጥቅሙ ማን እንደሆነና ለማን እንደሚከፈል ያልታወቀ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

<u>የተጣራ ሃብት ሂሳብ</u>

3. በፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6 ቁጥር 2 ፊደል ለ መሰረት የእያንዳንዱ የሂሳብ መደብ እንቅስቃሴ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን ዴቢትና ክሬዲት ጠብቆ መያዝ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት እያንዳንዱ ሂሳብ መደብ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን የጠበቀ መሆኑ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የተጣራ ሀብት (Net Asset/ Equity) በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበት ሚዛን ክሬዲት ሆኖ ሳለ በሰኔ 30/2014 በቀረበው የመዝጊያ ሂሳብ ሪፖርት ላይ በሂሳብ መደብ 7111101 ብር 439,543,104.88 ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን በዴቢት የሚታይ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 3 ከተገለፁት በስተቀር የመ/ ቤቱ የሂሳብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውን ገቢ የተከፈለውን ወጪና የበጀት አጠቃቀም በአጥጋቢ ሁኔታ ያሳያሉ፡፡

<u>ህጋዊነትን ያልተከተሉ ጉዳዮች (Compliance Matters)</u>

<u>ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

4. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 4 ፊደል ለ መሰረት ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ፤ እንዲሁም ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብለት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ፣ በመመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 16 ንኡስ አንቀጽ 4 መሰረት ደግሞ ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት መመሪያው

ያዛል። ይሁን እንጂ የ2014 በጀት ዓመት የተሰብሳቢ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፣ በሂሳብ መደብ 5217109 (4210) ብር 670,720.00 ለትግራይ ክልል የተላከ የድጎማ ሂሳብ መሆኑ በኦዲት ታውቋል።

ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች(Emphasis matter)

5. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት የሂሳብ አያያዝ እና አወቃቀር ስርዓት መሰረት ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ ኮዶችን /ቻርት ኦፍ አካውንት/ መሰረት ያደረገ የአሰራር ስርዓት ተግባራዊ መሆን እንዳለበት ይገልፃል።ይሁን እንጂ የጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚህ መሰረት መመሪያውን ተከትሎ ምዝገባ ማካሄዱን ለማረጋገጥ የተለያዩ ወጪዎችን በናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተለያዩ ቀናት እና በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥሮች በድምሩ ብር1,302,758.77 ክፍያ ሲፈጸም በተፈቀደ በጀትና የወጪ ሂሳብ መደብ ሊመዘገብ ሲገባ የሂሳብ መደቡን ያልጠበቀ መሆኑ በኦዲት ታውቋል ።

6. በፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 መርሆዎች 6 ቁጥር 2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግሥት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ይገልጻል።እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የበጀት አስተዳደር አጠባበቅ እና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 12 የመንግሥት ገንዘብ ክፍያ ወይም ወጪ ሊደረግ የሚችለው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ ነው።በዚህ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የ2014 በጀት ዓመት በሥራ ላይ የዋለውና ያልዋለው በጀት ለማነጻጸር ኦዲት ሲደረግ፦ በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በ2014 በጀት ዓመት ለየፕሮግራሞቹ የተመደበው የመደበኛ በጀት ሂሳብ በአግባቡ ስራ ላይ ከዋለው ሂሳብ ጋር ሲነጻጸር በተመለከቱት አንዳንድ የወጪ አርዕስቶች ከ10% በላይ ብር 61,471,051.33 ያልተጠቀሙበት በጀት የተገኘ መሆኑ በኢዲቱ ተረጋግጧል።

ሌሎች ጉዳዮች(Other matter)

የንብረት አያያዝና አጠባበቅ በተመለከተ

7. የፌደራል መንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል 2 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 ከፊደል ሀ-ሰ የመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነቶች በሚለው ሥር፤ ለንብረት የሥራ ክፍል በሰው ኃይልና አደረጃጀት ትኩረት መስጠት፣የመንግሥት ንብረት ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ አገልግሎት እንዲሰጥ ሥርዓት መዘርጋት፣የመንግሥት ንብረት ላይ ጉድለት መታየቱ በኦዲተሮች ወይም በሌላ አካል ሲረጋገጥ ንብረቱ በምርመራው መሠረት በዓይነት ወይም በገንዘብ እንዲተካ ማድረግ፣ዓመታዊ እና እንደ አስፈላጊነቱ ድንገተኛ የንብረት ቆጠራ እና የስቶክ ምርመራ እንደ ንብረቱ ዓይነት የጊዜ ገደብ በማስቀመጥ እንዲካሄድና ሪፖርት እንዲቀርብ ማድረግ፣ በዚህ መመሪያ የተገለፁትን ሌሎች ተግባሮች በበላይነት መከታተልና ማስፈፀም›› እንዳለበት፤ እንዲሁም የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ታህሳስ 2000 ዓ.ም ባወጣው የመንግስት ቋሚ ንብረት አስተዳደር ማንዋል /ጎፋም/ ንብረቶችን በልዩ ሁኔታ ለመለየት እንዲያስችለን፤በቀላሉ ለማግኘት እንድንችልና በቋሚ ንብረቶች ላይ ያሉትን መረጃዎች ለመተንተን እና ለማጠቃለል እንድንችል ቋሚ ንብረቶች ምክንያታዊና ሥርዓት ባለው መንገድ ለንብረቶች ቁጥር መስጠት እንዳለበት መመሪያው ያመለክታል፤ የቋሚና የአላቂ ንብረት አያያዝና አጠባበቅ በተመለከተ ኦዲት ሲደረግ የቋሚ ንብረት ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ከመዝገብ ጋርያልተመሳከረ (ያልተመዛዘና) መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

ተሽከርካሪን በተመለከተ

8. የፌዴራል መንግስት የተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ክፍል 2 አንቀጽ 6 ተራ ቁጥር 1-3 ከሀ-ሰ ስለመንግስት ተሽከርካሪዎች የሕይወት ታሪክ ምዝገባ በሚለው ስር ‹‹የመንግሥት መ/ቤት በግዥ፣በስጦታ፣በዝውውር…ወዘተ ተረክቦ ለሚጠቀምበት ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የተለየ የግል ማህደር በመክፈት በማህደሩ ውስጥ ቢያንስ የሚከተሉት መረጃዎች መዝግቦ ይይዛል፤ የተሽከርካሪውን ዓይነትና ሞዴል፣ የጭነቱ ልክ (በሰው፣ በኩንታል፣ በኪዩቢክ ሜትር ወይም በሊትር ተለይቶ)፤ የቻንሲና የሞተር ቁጥሮች፣ የሚጠቀመው የነዳጅ ዓይነት፤ የተገዛበት ወይም በመ/ቤቱ ባለቤትነት ሥር የዋለበት

ቀንና ዓመተ ምህረት፤የተሽከርካሪው ዋጋ እና የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ቁጥር መያዝ እንዳለበት መመሪያው ያዛል ፤ እነዚህ የተጠቀሱት መረጃዎች በበቂ ምክንያት ተሟልተው ያልተገኙ እንደሆነ ባሉት መረጃዎች መሰረት ርክክብ ከተፈጸመ በኃላ ተጠቃሚው መ/ቤት ያልተገኙትን መረጃዎች ዝርዝርና ምክንያት በተሽከርካሪው የህይወት ታሪክ ውስጥ መዝግቦ ይይዛል፣ ያልተሟሉትን መረጃዎችም ተከታትሎ እንዲሟሉ ይገልጻል፡፡እያንዳንዱ የመንግስት ተሽከርካሪ የህይወት ታሪክ መዝገብ የተሽከርካሪው ርክክብ ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ እስኪወገድ ድረስ በኪሎ ሜትር የሚጠቀመውን የነዳጅ፤ ዘይት፤ እና ቅባት ፍጆታ መጠን ፤ የጥገና ወጪ፤ የተጓዘው ኪ/ሜ መጠን በእነማን ስር እንደነበር ….ወዘተ እና ሌሎችም አካቶ መያዝ እንዳለበት ይገልጻል ፡፡ በዚህ መሰረት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት 41 ተሽከርካሪ መኪናዎች በ2014 በጀት ዓመት ተሽከርካሪዎቹ የተጓዙበት ኪሎ ሜትርና የተጠቀሙት ነዳጅ በአግባቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ተሽከርካሪዎቹ በአንድ ሊትር ነዳጅ ምን ያህል ኪሎ ሜትር እንደተጓዙ / normalization/ ለማረጋገጥ እና ሌሎችንም ክፍተቶች የተሽከርካሪ ኦዲት ሲደረግ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- ተሽከራካሪዎች በተቀዳላቸው ነዳጅ መጓዝ ከነበረባቸው ኪሎ ሜትር መሰረት ሲለካ 7 ተሽከርካሪዎች በመብለጥ 28 ተሽከርካሪዎች ደግሞ በማነስ የሚታይ መሆኑ፤
- በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተሽከርካሪ ዝርዝር ውስጥ የሁለት መኪና ኢት 4-03938፤ ኢት4-04230፤ ተሽከርካሪው የተመረተበት ዓመተ ምህረት ያልተመዘገበ መሆኑን ፤
- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ንብረት የሆነ ኢት 4-05024፤ኢት4-05297፤ኢት4-00962 ብዛት 3 ተሽከርካሪው በሊትር የሚጓዘው ርቀት/ ኖርማላይዜሽን / normalization /በሶስተኛ ወገን የተረጋገጠ መረጃ የሌላቸው መሆኑንና በመረጃ የተደገፈ አለመሆኑ ፤
- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ንብረት የሆነ 4 መኪና ኢት 4-03938 ፤ኢት4-20086፤.4-32468፤ኢት4-20090፤ኢት4-20096 የሊብሬ ቁጥር ያሌለ መሆኑን ፤
- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ንብረት የሆነ 1 መኪና ኢት 4-20085 የሞተር ቁጥር ያሌለ መሆኑን ፤

- የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ንብረት የሆነ 1 መኪና ኢት 4-20082 የሐምሌ ወር 2013 እስከ ሰኔ ወር 2014 ጌጅ የማይሰራ መሆኑን ፤
- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ንብረት የሆነ 8 መኪና ኢት 4-20076፤ኢት 4-20078፤ኢት 4-20081፤ኢት 4-20094፤ ኢት 4-20096፤ ኢት 4-20411፤ኢት 4-05297 እና ኢት 4-31335 ጋራጅ ለጥገና ለምን ያህል ጊዜ እንደቆሙ ዝርዝሩ የማይታወቅ መሆኑን ፤
- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ንብረት የሆነ 1 መኪና ኢት 4-04138 ግቢ በብልሽት የቆመ መሆኑን ፤
- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ንብረት የሆነ 108 መኪና ሊብሬ ደብተር ያለው ሲሆን የ67 መኪና የነዳጅ አጠቃቀም እና በኪሎ ሜተር ምን ይህል እንደሚሄዱ ከትራስፖርት ክፍል ሙሉ ማስረጃ ዝርዝር ማግኘት ያልተቻለ መሆኑን፤

<u>**የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አስተዳደር በተመለከተ**</u>

9. በፌዴራል መንግስት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 7 ተራ ቁጥር 4 ላይ ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው

   አካላትስለመስሪያአስፈላጊውንመረጃለመሰብሰብ፤ለመመዝገብ፤ለማከናወን፤ለማጠቀላልልእናሪፖርትለማድረግእንዲያስችላቸው በኮምፒወተር በታገዘ የመረጃ ስርዓት ላይ ተስማሚ ቁጥጥሮችን መዘርጋትና መጠበቅ አለበት ይላል፡፡በዚህ መሰረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የኢንፎርሜሽ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት አደረጃጀትና የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ሲታይ፣የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ የመረጃ ሚስጥራዊነት፣ታማኝነት እና ተገኘነት/ደህንነት ለማረጋገጥ በህጋዊነት የፀደቀ ኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ደህንነት መመሪያ የሌለ መሆኑ፣ እንዲሁም በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዙሪያ አካላዊ ተደራሽነት የሚፈትሹ ፖሊሲዎች የሌሉ መሆኑን እና የፌዱራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ስትራቴጂ የእሳት ማጥፊያ ሥርዓት እና የእሳት ማጥፊያዎች የሌለ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

የውስጥ ኦዲት ክፍልን በተመለከተ

10. የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 970/2008 ክፍል2 አንቀፅ 6/ለ የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች በመ/ቤቱ የተቋቋመው የውስጥ ኦዲት ሥርዓት ተገቢ እና በቂ የሰለጠነ የሰው ኃይል ያለው መሆኑን፣የውስጥ ኦዲትን በነፃነት፣ውጤታማ፣ፈጣንና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ መከናወኑን ማረጋገጥ እንዳለበት ተደንግጓል።እንዲሁም የፌዴራል መንግሥት የውስጥ ኦዲት መመሪያ ቁጥር 7/2003 አንቀጽ 8/2 የውስጥ ኦዲት የሥራ ክፍል ተገቢው የሙያ ብቃት፤ዕውቀትና ክህሎት ባላቸው ባለሙያዎች መደራጀት እንዳለበት ይገልፃል።በዚህ መሠረት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እያከናወነ መሆኑን ኦዲት ሲደረግ ፤

- በሥራ ክፍሉ መዋቅር መሠረት 15 የሰው ኃይል እንደሚያስፈልገው የተገለጸ ቢሆንም አሁን የሥራ ክፍሉ 8 የሰው ኃይል ብቻ የተሸፈነ መሆኑ እና ቀሪው 7 የሰው ኃይል ያልተሟላ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል::
- በዕቅድ የተያዙ ፋይናንስና ፔሮፎርማስ ሥራዎች ያልተከናወኑ መሆኑ፤
- የውስጥ ኦዲት በጠቅላይ ፍርድ ቤት እና በከፍተኛ ፍርድ ቤት አንድ የኦዲት ቡድን ብቻ መሆኑን፤
- የተቋሙ የሥራ አመራርም ከሥራ ክፍሉ በዕቅድ የተያዙ የኦዲት ሥራዎች በሰው ኃይል ዕጥረት አለመቅረብ በሚከሰቱ ግድፈቶች ላይ ወቅታዊ እርምጃ ለመውሰድ የማያስችል መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል።

የክትትል ኦዲት

11. የፌዴራል ዋና ኦዲተር በ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ መግለጫዎችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ የተወሰደባቸውና ያልተወሰደባቸው ግኝቶች ሁኔታ ሲጣራ፡-

    በኦዲት አስተያየቱ መሰረት <u>በቁጥር ደረጃ</u> ከተገለጹት የአሰራር ክፍተቶች ውስጥ 100 % እርምጃ የተወሰደ <u>በገንዘብ ደረጃም</u> እርምጃ ሊወሰድበት ከሚገባው አጠቃላይ የገንዘብ መጠን ውስጥ 100 % እርምጃ አልተወሰደበትም:: ዝርዝሩ ቀርቧል፡፡

- ለአግባብ ለማበረታቻ እና ለስጦታ ዕቃዎች መግዣ የተከፈለ ብር 45,000.00 መኖሩ፤
- አለአግባብ ወጪ የሆነ የትርፍ ሰዓት ክፍያብር 22,133.47፤መኖሩን፤

  ያለአግባብ ለነዳጅ የተከፈለ ብር 83,786.40፤ መኖሩን በኦዲት ታውቋል፡፡

ከሰላምታ ጋር

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት